# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 344 ታህሳስ 3 2007 ገጽ


ከህወሓት አገዛዝ መገላገል የሚቻለው ተገዶ ሲወገድ ብቻ ነው። ህወሓት እንዲወገድ ደግሞ የመጨቆኛ አቅሙ መዳከም ይኖርበታል። ህወሓትን የማስወገጃ አማራጭ መንገዶች ብዙ ሲሆኑ ተቀናጅተው ቢሠሩ የበለጠ ውጤታማ ይሆናሉ ብለን እናምናለን፤ "ሁለገብ ትግል" የምንለው የትግል ስልት ጭብጥ ይህ ነው። "እምቢ ለነፃነቴ" ብሎ የተነሳ ሕዝብ ህወሓትን ምን ያህል እንደሚያስደነግጥ በተደጋጋሚ ታይቷል።

ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ላይ የወሰደዉ አረመኔያዊ እረምጃ ተወገዘ

እብሪተኛው ወያኔ የተቃዋሚ ፓርቲዎች በጥምረት ባቋቋሙት የዘጠኙ ፓርቲዎች ትብብር አማካኝነት ለህዳር 27 ተጠርቶ በነበረው የአዳር የአደባባይ የተቃውሞ ሰልፍ ላይ የአገዛዙ አጋዚ ፓሊሶች ከቅጥረኛ የደህንነት አባላት ጋር በመሆን በፓርቲዎቹ አመራሮች፤ አባላት እንዲሁም በተቃውሞው ለመሳተፍ በተገኙ ኢትዮጵያውያን ላይ የወሰዱት እጅግ አረመኔያዊ የድብደባ፤ ወከባ እና የእስር እርምጃ በአገር ውስጥ እና በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ማስቆጣቱ ታውቋል። የእብሪተኛው ወያኔ አጋዚ ፓሊሶችና የደህንነት አካላት በጥምረት በወሰዱት ከፍተኛ የሆነ ሐይል በተቀላቀለበት እርምጃ በርካታ የትብብሩ አመራሮችና አባላት እንዲሁም ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ የተቃውሞው ተሳታፊ ግለሰቦች ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸው፤ ህክምና ተነፍገው በከፋ ስቃይ ላይ እንደሚገኙ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በጅምላ ወደ እስር ከተጋዙት ከ 500 በላይ ሰዎች ውስጥ ፋሺስታዊው አገዛዝ በተለይ የትብብሩ አመራሮችንና አባላት ከፍተኛ ቀዝቃዜ ባለበት የጨለማ ክፍል ውስጥ አጉሯዋቸው ከፍተኛ የሆነ ድብዳባ እየተፈጸመባቸው እንደሚገኝ ለማወቅ ችለናል። የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በተለይ የትብብሩ አመራሮችና አባላት ላይ የተለመደ የፈጠራ ክስ በመለጠፍ ለማሰር እንቅስቃሴ መጀመሩም የታወቀ ሲሆን የተወሰኑ አመራሮችና አባላት የፈጠራ ክስ ቀርቦባቸው የካንጋሮው ፍርድ ቤት መቅረባቸው ታውቋል። ወደ ተቃውሞ ስፍራው አብዮት አደባባይ ከተለያዩ አቅጣጫዎች እያመሩ የነበሩ ሂጃብ የለበሱ በርካታ የእስልምና እምነት ተከታይ እህቶቻችን በአጋዜዎች አሰቃቂ ድብደባ ተፈፅሞባቸው ታፍነው ወዳልታወቀ ስፍራ መወሰዳቸውም ታውቋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ይህ አረመኔያዊ ድርጊት አገዛዙ በሙስሊም እምነት ተከታዮች ላይ የከፈተው የጥፋት ዘመቻ አንዱ ማሳያ እንደሆነ በስፋት እየተነገረ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል። ... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## አሜሪካ ኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉ ዜጎቿ ከፍተኛህ ጥንቃቄ እንዲወስዱ አበክራ አሳሰበች

የአሜሪካ መንግስት በኢትዮጵያ በአራቱም የአገሪቱ ማዕዘናት እየተቀጣጠለ ያለው የህዝባዊ ተቃውሞና እምቢተኝነት እንቅስቃሴ ወደ ህዝባዊ አመጽ እያመራ እንደሚገኝ በመጠቆም በአገሪቱ የሚገኙ ዜጎቿ ለደህንነታቸው ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲወስዱና እንቅስቃሴያቸውን እንዲገድቡ መቀመጫውን አዲስ አበባ ባደረገው ኢንባሲ አማካኝነት ማስጠንቀቂያ አውጥቷል። የአሜሪካ መንግስት በኢንባሲው አማካኝነት ያወጣው ማስጠንቀቂያ እንደገለጸው በኢትዮጵያ በመጭው ግንቦት ወር ይካሄዳል ተብሎ የሚጠበቀው ምርጫ ጋር ተያይዞ በየትኛውም የአገሪቱ አካባቢ በማንኛውም ጊዜ ያለ አገዛዙ ፍቃድ ህዝብ ለተቃውሞ በነቂስ ወደ አደባባይ ሊወጣ እንደሚችል በመጠቆም የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በህዝብ ዘንድ እያደረሳቸው የሚገኙት በደሎችና ጭቆናዎች ገደባቸውን እያለፉ በመምጣታቸው የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ህዝባዊ አመጽን ይወልዳሉ ሲል የአሜሪካ ዜግነት ያላቸው ግለሰቦች ከተቃውሞ ትዕይንቶች ራሳቸውን እንዲያርቁ አበክሮ አሳስቧል። ኢንባሲው በማያያዝም ቀድም ሲል በሶማልያ የመሸገው አልሸባብ በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ሊወስድ ይችላል በሚል ያወጣውን ቅድመ የጥቃት ማስጠንቀቂያ በማስታወስ ዜጎች አደጋዎች ሊከሰቱ ከሚችሉባቸው የምዕራባውያን መስሪያ ቤቶች፤ የጉጅሌው ወያኔ ተቋማት፤ የህዝብ መገባባያ ቦታዎች እንዲሁም ከአምልኮ ስፍራዎች የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች ከግንዛቤ እንዲከቱ ሲል በድጋሚ አሳስቧል። በኢትዮጵያ የሚኖሩ የአሜሪካ ዜግነት ያላቸው ዜጎች ሁሉ ለጥንቃቄ እና ለደህንነት ሲባል ከፍተኛ አደጋ አንዣቦ ከሚገኝባቸው የኢትዮጵያ አካባቢዎች ማለትም የኢትዮ ኬኒያ ድንበር ሞያሌ አካባቢ፤ ከኢትዮ ኤርትራ ድንበር አቅራቢያ ሰሜናዊ ሽሬ እንደ ስላሴ፤ አክሱም፤ ከአክሱም ወደ አዲግራት መንገድ፤ በደሴ ወሎ ወደ ጋላፊ የኢትዮ ጅቡቲ ድንበር፤ ወደ ሶማሌ ምስራቅ ኢትዮጵያ እና ወደ ጋምቤላ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች እንዲያቆሙ አብክሮ አሳስቧል።

## ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች እርስ በርስ ተፋጥጠዋል፤ ድርጅታቸዉ ህወሓት የመሰንጠቅ አደጋ ተጋርጦበታል

በዘረኞቹ የህወሕት ቱባ ሹማምንት መካከል በየ ጊዜየው የተለያዩ አለመግባባቶች እየተከሰቱ በተለያዩ ጎራዎች ተሰልፈው መተረማመሳቸው መዘገቡ የሚታወስ ሲሆን ከሰሞኑ እየተደረገ ባለው የውስጥ ስብሰባ ዳግም ሁለት ቦታ የተከፈሉት የሕወሐት አመራሮች ልዩነቶቻቸው ሰፍተው፤ ፍጥጫው ዳግም አገርሽቶ እየተወዘጋገቡ እንደሚገኙ የውስጥ ምንጮቻችን ገለፁ። በስብሃት እና በረከት እየተመሩ እንደሆነ በታወቁት ሁለቱ ቡድኖች በተለይ ሕወሓት በተመለከተ ከመቼውም ጊዜ እጅግ የሰፋ አነጋጋሪ የሆኑ የአቋም ልዩነቶችን መያዛቸውን እና፤ ወደ ስምምነት ሊደርሱ አለመቻላቸው ታውቋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የሁለቱም ጐራ ፖለቲካዊ ግብ አንዱ ሌላኛውን ገፍትሮ ከሜዳው ማስወጣትና ፓርቲውን ብሎም አገሪቱን በፈላጭ ቆራጭነት ለመቆጣጠር ያለመ እንደሆነ ምንጮቻችን ጠቁመዋል። በዘረኞቹ የህወሓት ሹማምንት በተለኮሰው ስር የሰደደ ፖለቲካዊ ፍጥጫ መረጃው የደረሰቸው ታችኞቹ ቅጥረኛ ካድሬዎች ጭምር ለሁለት ተከፍለው ሲነታረከ መሰንበታቸውንም ለማወቅ ተችሏል። በፓርቲው አባላት የተፈጠረው አለመግባባት ተከትሎ የነገሰው ፍጥጫ ያሰጋቸው ገለልተኛ የሆኑ ጥቂት አካላት የአስታራቂነት እንቅስቃሴ ቢያደርጉም በሁለቱም ቡድኖች በኩል በሚታየው አክራሪ አቋም ምክንያት ተስፋ ሰጪ ሁኔታ እንደማይታይ ምንጮቻችን አስታውቀዋል። አሁንም ድርድሩ መቀጠሉን ምንጮቹ አልሸሸጉም። የበላይነትን እየያዘ ነው የተባለው በስብሃት ነጋ የተደራጀው እንዲሁም በደብረፂዮን የሚመራው ቡድን አብዛኞቹን የህወሓት የማ/ኮሚቴ አመራሮችን በዙሪያው ያሰባሰበ ሲሆን ከነዚህም፥ አዲስአለም ባሌማ፣ አርከበ እቁባይ፣ ቅዱሳን ነጋ፣ ፈትለወርቅ፣ ፀጋዬ በርሄ፣ አባዲ ዘሙ፣ ሃ/ኪሮስ ገሰሰ፣ ተ/ብርሃን...በዋንኛነት እንደሚገኙበት ለማወቅ ችለናል። ... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## በደቡብ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች የነገሰውን ውጥረት ተከትሎ ፍተሻው ከወትሮው በተለየ መልኩ መጨመሩ ታውቀ

በደቡብ ክልል የሚገኙ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች በተለያዩ ጊዜያት አንስተዋቸው የነበሩና ፈጽሞ እልባት ሊያገኙ ያልቻሉ ከመብትና መልካም አስተዳደር ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን መጠየቅ መጀመራቸውን ተከትሎ በክልሉ ከፍተኛ ውጥረት መንገሱ ታውቋል። በተለይ ከሰሞኑ በዳውሮ ዞን ህዝባዊ ጥያቄው ዳግም ማገርሸቱ የታወቀ ሲሆን በአገዛዙ የመሳሪያ ሐይል ተዳፍኖ የቆየው በጋሞ ጎፋ ዞን የቁጫ ወረዳ የመብት ጥያቄ መቀስቀሱም ታውቋል። ከመብት ጥያቄው ጋር በተያያዘ አንዳንድ የአካባቢው ነዋሪዎች በቅጥረኛ ፖሊሶች እየደረሰባቸው የሚገኘውን ወከባ ለመሸሽ ሌሊቱን የሚያሳልፉት ጫካ ውስጥ መሆኑ የታወቀ ሲሆን ቅጥረኛ ፖሊሶች ሌሊት ቤት እየሰበሩ በመግባት ፍተሻ እያደረጉ እንደሚገኙ ለማወቅ ችለናል። በተያያዘ ዜና በፋሽስቱ ወያኔ እኩይ ሴራ በቦረናና በቡርጂ ማህበረሰብ አባላት መካከል ግጭት ተቀስቅሶ ከ4 ሺ በላይ ነዋሪዎች ቀያቸውን ጥለው መሸሻቸው መዘገቡ የሚታወስ ሲሆን ከሰሞኑ እልባት ያላገኘው የሁለቱ ጎሳዎች ግጭቱ ዳግም ማገርሸቱ ታውቋል። ከግጭቱ ማገርሸት ጋር ተያይዞ እስከ ትናንት ድረስ ከ1 ሺህ በላይ ቡርጂዎች አካባቢውን ለቀው መሰደዳቸው ታውቋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በክልሉ የነገሰውን ከፍተኛ ውጥረት ያሰጋው የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ ቁጥር ያለው አጋዚ ጦር በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች ማስፈር መጀመሩን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በክልሉ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚታየው የመኪና ፍተሻ መጨመሩንም ለማወቅ ተችሏል።የአገዛዙ ቅጥረኛ ፖሊሶች በተለይ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የህዝብ ማመላለሻ መኪኖችን በማስቆም ፍተሻ እያደረጉ ከመሆኑም በላይ ለተሳፋሪው ከየት እንደመጡ፤ ወደየትና ለምን እንደሚሄዱ እየጠየቁ ሲሆን የሰዎች ኪሶች በመግባት ፍተሻ እያደረጉ እንደሚገኙ ታውቋል። በሽተኞችንና ህጻናትን የታቀፉ እናቶች ሳይቀሩ ፍተሻ በሚል ፖሊስ ጣቢያ ታጉረው ለረዥም ሰአታት እየተጉላሉ እንደሚገኙም ለማወቅ ችለናል።

## በሰላማዊ ተቃዋሚዎች ላይ የደረሰውን ጥቃት እናወግዛለን !!!

በአብዛኛው በወጣት ወንዶችና ሴቶች የተገነባው ሰማያዊ ፓርቲ አባል የሆነበት የዘጠኝ ፓርቲዎች ኅበረት፣ "ነፃነት ለፍትሃዊ ምርጫ" የተሰኘ የአንድ ወር መርሀ ግብር አውጥቶ፤ ችግሮችን ተጋፍጦ አብዛኛውን ተግባራዊ አድርጓል። የመርሀ ግብሩ አቢይ አካል የነበረውና በህዳር 27 እና 28 ሊከናወን ታድቆ የነበረው የ24 ሰዓት የአደባባይ ተቃውሞ ግን በአገዛዙ የኃይል እርምጃ ምክንያት በታቀደው መንገድ ሊከናውን አልቻለም። የህወሓት ቅልብ የሆኑት ሲቪል የለበሱ ሰላዮችና የፌደራል ፓሊስ በተቃውሞው ተሳታፊዎች ላይ ኢሰብዓዊ የሆነ ጥቃት ፈጽመዋል።

ከጅምሩ፣ የፓርቲዎቹ ኅበረት የተቃውሞ ማሳወቂያ ደብዳቤውን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለማስገባት የገጠመው ችግር የህወሓት አገዛዝ የመንግሥትን መዋቅር ለፓርቲ ሥራ፤ የመንግሥት ተቀጣሪዎችን ደግሞ እንደ ህወሓት አገልጋዮች የሚጠቀምባቸው መሆኑ አንዱ ማሳያ ሆኗል። ሰላማዊ ሰልፍ እንደሚያደርጉ ማሳወቅ የፈለጉት ፓርቲዎች ህወሓት የዘረጋውን አፋኝ ሥርዓት የሚታገሉ በመሆናቸው ብቻ ደብዳቤዓቸውን የሚቀበል እንኳን አጥተው ተጉላልተዋል። ለሰልፉ ቅስቀሳ ማድረግም በራሱ እንደ ወንጀል ተቆጥሮ ወጣቶች ተንገላተዋል፣ ተደብድበዋል፣ ታስረዋል። ያም ሆኖ ውጣ ውረዶች ታልፈው ቅዳሜ ህዳር 27 ቀን 2007 ዓ. ም. ደረሰ።

የኅበረቱ አመራሮች፣ አባላት፣ ደጋፊዎችና ጥሪውን የሰማ ሕዝብ ወደ መስቀል አደባባይ ማምራት ሲጀምር ሲቪል የለበሱ የአገዛዙ ታጣቂዎች እና ፌደራል ፓሊሶች ከሰንደቅ ዓላማዎችና መፈክሮች ባለፈ አንዳች ነገር ያልያዙትን እድሜያቸው ከሃያዎች ያልዘለሉ ውድ የኢትዮጵያ ልጆችን ደብድበዋል፤ ብዙዎቹም አፍነው በአሰቃቂ ሁኔታ እያንገላቱ ወደ እስር ቤቶች ወስደዋል። ወጣቶች ተወልደው ባደጉበት አገር፤ ስሜታቸውን በነፃነት ለመግለጽ በመድፈራቸው ብቻ በጭካኔ ተረግጠዋል፤ ተፈንክተዋል፤ እጅና እግሮቻቸው ተሰብሯል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህ የህወሓትን ፋሺስታዊ እርምጃ አጥብቆ ይቃወማል። ግንቦት 7፣ ህወሓት ከስልጣን እስካልተወገደ ድረስ እንዲህ ዓይነቱን ፋሺስታዊ ተግባር መፈፀሙን የማይተው እኩይ ኃይል እንደሆነ ያውቃል፤ በዚህም ምክንያት የትግላችን ግብ ህወሓትን ማስወገድና በምትኩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይሁንታ ያገኘ መንግሥት መመሥረት መሆን ይኖርበታል ብሎ ያምናል፤ ለዚህም ይታገላል።

ግንቦት 7፣ ህዳር 27 ቀን 2007 ዓ.ም. "መብቶቻችንን በህወሓት ዘረኛ አምባገነኖች አናስነጥቅም" በማለት አደባባይ የወጡ ወጣቶችን ጽናት ያደንቃል። ህወሓት የሚለውን ሳይሆን የይስሙላ ህጉ የፈቀደላቸውን ለማድረግ በመድፈራቸው በህወሓት የህግ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ የሚደረገውን ትግል አንድ እርምጃ ወደፊት አራምደውታል።

እያንዳንዱ የፓለቲካ ድርጅት ከዚህ ኩነት የሚወስዳቸው ተጨማሪ ትምህርቶች ቢኖሩም የሚከተሉትን ነጥቦች ብዙዎችን ያስማማሉ ብለን እናምናለን።

1. ህወሓት በምንም ዓይነት ቢሆን የያዘውን ስልጣን ለሕዝብ ፈቃድ ማስገዛት አይፈልግም፤
2. ህወሓት አገራችን ወደ ትርምስ እየገፋት እንደሆነ ግልጽ እየሆነ መጥቷል፤
3. ስልጣኑን የሚያሳጣው ከመሰለው እና አቅሙ እስካለው ድረስ ዘግናኝ እርምጃዎችን ከመውሰድ አይመለስም፤

ከህወሓት አገዛዝ መገላገል የሚቻለው ተገዶ ሲወገድ ብቻ ነው። ህወሓት እንዲወገድ ደግሞ የመጨቆኛ አቅሙ መዳከም ይኖርበታል። ህወሓትን የማስወገጃ አማራጭ መንገዶች ብዙ ሲሆኑ ተቀናጅተው ቢሠሩ የበለጠ ውጤታማ ይሆናሉ ብለን እናምናለን፤ "ሁለገብ ትግል" የምንለው የትግል ስልት ጭብጥ ይህ ነው። "እምቢ ለነፃነቴ" ብሎ የተነሳ ሕዝብ ህወሓትን ምን ያህል እንደሚያስደነግጥ በተደጋጋሚ ታይቷል። ህዳር 27ን መንደርደሪያ አድርገን በመውሰድ ከዚህ በተሻለ ለተደራጀ ሕዝባዊ እምቢተኝነትና አመጽ ራሳችን እናዘጋጅ።

በዚህ አጋጣሚ ግንቦት 7፣ ለመከላከያ ሠራዊት እና ፓሊስ አባላት ተደጋጋሚ ጥሪዎችን ማድረግ ይሻል። የመከላከያ ሠራዊት እና ፓሊስ አባላት እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ በህወሓት ዘረኛና አምባገነን አገዛዝ የተበደላችሁ መሆኑን እናውቃለን። የህወሓት ሹማምንት ከሆኑ አዛዦቻችሁ መላቀቅና ራሳችሁን ነፃ የማውጣት ኃላፊነት የወደቀው በእናንተው በራሳችሁ ላይ ነው። ሠራዊቱ ራሱን በራሱ ነፃ ማውጣት ይኖርበታል። የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ህወሓት መወገዱ የማይቀር በመሆኑ ሠራዊቱ ራሱን ነፃ አውጥቶ ከሕዝብ ጋር ካልወገደ እጣ ፈንታው የተሸነፈ ሠራዊት መሆን ነው። ከዚህ በላይ የሠራዊቱ አባል እየደበደበ ያለው የራሱን ልጅ፣ ወንድሙን ወይም እህቱን እንደሆነ ይወቅ። ይህ ወሳኝ ጊዜ ነው እያንዳንዱ የሠራዊቱ አባል በግል ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ሊሰማው ይገባል።

በሁሉም ዓይነት የትግል ዘርፎች የኢትዮጵያ ወጣቶች በስፋት እየተቀላቀሉ መሆኑ ተስፋ ሰጪ ነው። ጊዜው የለውጥ ነው። የተለያዩ ስትራቴጂዎች ተደጋግፈው እንዲሄዱ መደረግ ያለበት ወቅት ላይ ነን። በህዳር 27 ቀን በህወሓት ቅልብ ሰላዮችና የፌደራል ፓሊሶች አማካይነት የደረሰው ጉዳትና የፈሰሰው ደም ለፍትህና ለነፃነት የተከፈለ ዋጋ ነው። ህመማችሁ ህመማችን፤ ትግላችሁ ትግላችን ነው። የተለያዩ መንገዶች ወደ ነፃነት አደባባይ እያመሩ ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !**

---

## ሰማያዊ ፓርቲ ትግሉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታወቀ

የሰማያዊ ፓርቲ ምክር ቤቱ ህዳር 30/ 2007 ዓም ባወጣው መግለጫ ኢትዮጵያ ዉስት በህዝብ ሙሉ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ዲሞክራሲያዊ ስርዐት እሲኪመሰረትና በህግ የበላይነት የሚያምን መንግስት እሰኪኖር ድረስ ትግሉ የሚጠይቀዉን መስዋዕትነት ሁሉ ለመከፍል ዝግጁ መሆኑን አሳወቀ። የወያኔ እስር፤ ድብደባና ማዋረድ ከትግሉ በፍጹም ፈቀቅ እንደማያደርጋቸዉ የተናገሩ የሰማያዊ ፓርቲ መሪዎች ትግሉ ተፋፍሞ መቀጠሉንና ህዝባዊ መሠረት መያዙን ተናገግረዋል።

"ሰማያዊ ፓርቲን ጨምሮ ዘጠኝ ትብብር የፈጠሩ ፓርቲዎች በህዳር ወር ያወጡት መርሐ ግብር አንድ አካል የሆነውን የ24 ሰዓት የተቃውሞ የአደባባይ ሰልፍ ለመተግበር ሥራ ላይ የነበሩ አመራሮች፣ አባሎቻችና ደጋፊዎቻችን ላይ አምባገነኑ ስርዓት በወሰደው የግፍ እርምጃ ምክንያት ከፍተኛ ድብደባ" እንደደረሰባቸውና በጨለማ ክፍል ውስጥ እንደተወረወሩ መግለጫው አስታውሷል።።ሽንት ቤትና ጋራዥ ውስጥ አባሎቻችን መታሰራቸው አልበቃ ብሎ በቤተሰብ እንዳይጠየቁ መደረጉ እንዲሁም በድብደባው ምክንያት ራሳቸውን የሳቱና ከፍተኛ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው አመራሮች፣ አባላትና ደጋፊዎቻች የህክምና አገልግሎት ማግኘት እንዳይችሉ መደረጉን የጠቀሰው የምክር ቤቱ መግለጫ፣ አገዛዙ ይህን ሁሉ ግፍ የሚፈጽመው ለሰላማዊ ታጋዮች ባለው ጥልቅ ጥላቻና ጭካኔ በተሞላበት እርምጃው ከትግሉ ያፈገፍጋሉ ከሚል ስሌት ነው ሰል ያክላል።

ሆኖም ይላል መግለጫው "እኛ ወደ ወደ ትግሉ ስንገባ ትግሉ ምን ያህል መስዋዕትነት እንደሚያስከፍል በሚገባ እናውቀዋለንና የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ የወሰደውና ወደፊትም ሊወስደው የሚችለው ከዚህ የባሰም አረመኔነት የተሞላበት እርምጃ ይበልጡን ያጠናክረናል እንጅ ከትግላችን ቅንጣት ያህል ወደኋላ እንድናፈገፍግ አያደርገንም ብሏል። ህወሓት/ኢህአዴግ የሰልፉን ተሳታፊዎች ደብድቦና አፍሶ ባሰረበት ወቅት "ምንም ችግር ሳይፈጥሩ በቁጥጥር ስር ውለዋል" እንዳላለ፣ ከስርዓቱ ቁጥጥር ያልወጣው የህግ አካል "መስቀል አደባባይ ላይ ንብረት ወድሟል።" በሚል ሌላ ክስ ማቅረቡ፣ ፓርቲያችንና ትብብሩ በጀመረው ሰላማዊ ትግል ህወሓት/ኢህአዴግ መደናገጡን የሚያሳይ መሆኑን ጠቅሷል። መግለጫው በመጨረሻም "በሀገራችን ህዝባዊ ሥርዓት ለማምጣትና በህግ የበላይነት የሚያምን መንግስት ለመመስረት በምናደርገው ትግል ሁሉ የሚጠበቅብንን መስዋእትነት ለመክፈልና ሀገራዊ ግዴታችንን ለመወጣት ዝግጁ" ነን ካለ በኋላ፣ "መስዋዕትነት ለመክፈል የተዘጋጀንለትና የምናከብረው ህዝብ ከጎናችን እንዲቆም ጥሪያችንን እናቀርባለን።" በማለት ደምድሟል።

በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ -ኢህአፓ ባወጣው እርምጃ በሰላማዊ ተቃዋሚዎች ላይ የተወሰደው እርምጃ "ነፃነት በልመና የማትገኝ መሆኑን ያረጋገጠ ብቻ ሳይሆን የወያኔ አገዛዝ በሕዝባዊ ትግል ከሥልጣን እስካልተወገደ ድረስ ቀጣይ ሊሆን እንደሚችልም በግልፅ ያሳየ ነው።" ብሎአል።ኢህአፓ የታሰሩት የድርጅት አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ሰላማዊ ዜጎች በአስቸኳይ እንዲፈቱ፡ ጉዳት ለደረሰባቸው ሁሉ አስቸኳይ የሕክምና አገልግሎት እንዲደርሳቸው ጠይቆ፣ ስልፉ የተደረገበት ዓላማ ግቡን እስኪመታ ድረስ ሳይቋረጥ ትግሉ መቀጠል ያለበት መሆኑንም አስታውሷል። ዘግይቶ በደረሰን ዜና ደግሞ በእስር ላይ የሚገኙት የትብብሩ አባላት የተወሰኑት በዋስ እንዲፈቱ መወሰኑ ታውቋል። ሶስተኛ ከታሰሩት ውስጥ ሜሮንንና ምኞትን ነጥለው እንዲወጡ ቢጠየቁም ሌሎች እስረኞች ግን ሁሉም ካልተፈቱ አንወጣም ብለዋል።

---

## የፈሪ ዱላ ነፃነትን አያስቀርም !

ህወሃቶች ኢትዮጵያን “ለመምራት” ያላቸው አቅም ተሟጦ አልቋል። ፍርሃት አቅላቸውን አስቷቸዋል። ፍርሃታቸው ጭካኔን ወልዷል። ይህ ጭካኔያቸው ወሰን አጥቷል። ልጥ ባዩ ግዜ እባብ እየመሰላቸው ልጡን በቆመጥ ሲደበድቡ ውለው ያድራሉ። ፍርሃት ያ ደካማ ማሰቢያቸውን ጥርቅም አድርጎ ዘግቶታል። የፈሪ ዓይን ማየት እንደማይችል፤ ጆሮውም መስማት እንደተሳነው ከህወሃቶች ተርድተናል።

እኛ ግን እንዲህ እንላለን ህወሃቶች ዓይናችው እያየ፤ ጆሮዋቸውም እየሰማ የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነቱን ይቀዳጃል። እውነት እውነት እንላችኋለን የነፃነቱ ግዜ እሩቅ አይደለም። ህወሃቶች ከነፍርሃታቸው ወደ መረጡት መቃብራቸው መውረዳቸው እንደማይቀር ቅንጣት ታክል ጥርጣሬ የለንም።

የኢትዮጵያ ህዝብ ምርጫ ነፃነት ነው።ይህን ነፃነት ከህወሃቶች እጅ ለምነን የምናገኘው አይደለም። ነፃነታችንን ታግለንና አሸንፈን የምንቀዳጀው ንፁህ ሃብታችን ነው። ይህን ንፁህ ሃብታችንን በቀማኞች አስነጥቀን ዝም ብንል እርግማን ይሁንብን ያሉ ኢትዮጵያዊያን እያደረጉ ያሉት ትግል ተስፋ ሰጪ ነው። በተለይም ወጣቶች እምቢ ለክብሬ፤ እምቢ ለነፃነቴ እምቢ ለማያውቁን ህወሃቶች ማለታቸውን ስናይ ተስፋችን ከመቸውም ግዜ በላይ ለምልሟል።

ህወሃቶች ኃላፊነት የሚሰማቸው ቢሆኑ ኑሮ “በሃሳባችሁ ባንስማም ልዩነታችሁን መግለፅ የምትችሉበትን መብት ለማስከበር እስከ ሞት ድረስ እንቆማለን” ይሉ ነበር። አለመታደል ሁኖ ህወሃቶች አገር፤ ህዝብ፤ ወገን የሚባል ቋንቋ በውስጣቸው የለም። ኢትዮጵያም አገራቸው አትመስላቸውም፤ ህዝቡም ወገናቸው እንደሆነ አይሰማቸውም። ህወሃቶች በወንድምና እህቶቻቸው አጥንት ላይ ቁመው ለኢትዮጵያና ለህዝቧ ጠላት መሆንን መርጠዋል። ለነፃነት ብለው በትግል ሜዳ የተሰው ጓዶቻቸውን ሞትም ከንቱ ሞት አድርገው አስቀርተውታል። ይሄ እርግማን ነው።ይሄ እርግማን ደግሞ አሁን ባሉት ህወሃቶች ብቻ የሚቆም ሳይሆን ወደ ልጅ ልጆቻቸው እንደሚሸጋገር ህወሃቶች ለማሰብ አቅቷቸዋል።

ህወሃት የስለጠነ ፖለቲካ አያውቅም። የነፃነትንም ትርጉም ሳያውቅ ነፃ አውጪ ነኝ ይላል። በአገሪቷ ጫንቃ ላይ መቆየት ብቻ የህልውናየ መሠረት ነው ብሎ ካመነም ቆይቷል። ይህን የህልውናየን መሠረት የሚነካ ሁኔታ ከተፈጠረም ጠመንጃየ መመኪያ ጉልበቴ ነው የሚል የማይናወፅ አቋምም ይዟል። ይህ አቋሙ አገሪቷ ከተጋረጡባት አደጋዎች መካከል አንዱ ሁኖ ይታየናል። የዚህ አቋም መዘዙ አሁን ባለው ትውልድ ብቻ የሚያበቃ አይደለም። ወደ ቀጣዩ ትውልድ ተሸጋግሮ የአገሪቷ ዜጎች በሠላም አብረው የሚኖሩበትን እድል እንደሚያበላሸው ህወሃቶች አያውቁም ማለት አይቻልም። ተደጋግሞ እንደተነገረው በህወሃቶች ዘንድ ትውልድ የሚባል ቋንቋ እንዲጠፋ በመደረጉ ለመጪው ትውልድ የሚተርፍ ቂም ትተው ለማለፍ ሳያቅማሙ እየሰሩ ይገኛሉ።

የኢኮኖሚ መዋቅሩ በእነርሱ ብቻ መያዙ ነገ ለእነርሱ ልጆች የደም እንጀራን እንደሚያተርፍላቸው እንዲገነዘቡ ማድረግ ተገቢ ይመስለናል።በህወሃቶች አስተሳሰብ ሌላውን የኢትዮጵያ ህዝብ ድሃ አድርገን ከያዝነው ከዕለት ጉርሱ አልፎ ሂዶ ነፃነትን ይጠይቀናል ለነፃነት የሚከፍለውንም ዋጋ ለመክፈል አቅም አይኖረውም የሚል ሙት ፍልስፍና መመሪያቸው ሁኗል። እኛ ብቻ በኢኮኖሚ ጎልበትን ሌሎቹን የእኛ ጥገኛ ካደረግን ለዘላለም ከነ ልጅ ልጆቻችን ነግሰን እንኖራለን የሚል ቅዥት ውስጥ ሁነው አገሪቷን ወደ ትርምስ እየወሰዷት እንደሆነ እያየነው ነው።ህወሃቶች ከእህል ውሃ የዘለለ ራዕይ እንደሌላቸው የሚታወቅ ነው። ራዕይ አልባዎች ተደራጅተው አገር መምራት ሲጀምሩ አገሪቷና ህዝቧ በሙሉ ራዕይ አልባ ይሆናሉ። መፅሃፍ እንደሚነግረን ደግሞ “ራዕይ አልባ አገር ይጠፋል” ይላል። የህወሃቶች ምኞት ይሄው ነው። እኛ ከሌለን ኢትዮጵያ አትኖርም የሚል ክፉ ምኞት።

### ኢትዮጵያዊያን ሆይ !

ህወሃት የጭለማን መንገድ መርጧል። ይሄ መንገዱም አገሪቷንና ህዝቧን ወደ መቀመቅ እየጨመራት ነው። አገሪቷን አስይዞ ከግል ኩባንያዎች ብድር እስከ መለመን ደርሷል። ቀጣዩ ትውልድ ከሚወርሰው ቂምና በቀል በተጨማሪ በእዳ የተያዘ ትውልድ ይሆናል። በቀላል አነጋገር ትውልዱ የባዕድ ተገዢ እንዲሆን ተፈርዶበታል። ህወሃቶች ለመጪው ትውልድ የሚሰጡት ስጦታ ባርነትን እንዲሁም ቂምና በቀልን እንጂ ነፃነትንና አብሮ መኖርን አይደለም።

እንግዲህ ህወሃቶችን አደብ ማስያዝ የዚህ ትውልዱ ግዴታ ይሆናል። ህወሃት ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ውሳኔ ሰጪነት ካልተወገደ በቀር በኢትዮጵያ መረጋጋት አይኖርም። ችጋርም አይጠፋም። የንፁህ ሰው ደም ከመፍሰስ አይቆምም። አገሪቷም በእዳ ላይ እዳ ከመጨመር አትመለስም።

ይህ ሁኔታ መቆም እንደሚኖርበት አሁን ሁሉም ተገንዝቧል። ይህ ሁኔታ ግን እንዲሁ በከንቱ የሚቆም አይሆንም። ለዚህ የሚከፈል የደም መሥዋዕትነት የግድ ሁኖብናል። ፍትህ፤ እኩልነት እና ነፃነት የደም ውጤቶች ናቸው። ያለ መሠዋዕትነት የሚመሠረት ፍትህ አይኖርም፤እኩልነትም ቢሆን የብዙዎችን መስዋዕትነት ይጠይቃል፤ የነፃነት ቀንዲል የሚለኮሰው በደም አቀጣጣይነት ነው። ህወሃቶች መሽቶ በነጋ ቁጥር የንፁህ ደም ያፈሳሉ። ዝም ያሉትም ሞት አልቀረላቸውም፤ የተናገሩትም የውርደት የሞት ፅዋቸውን እየተጎነጩ ነው፤ ሌሎቹም ከሞት በባሰ ሁኔታ በየማጎሪያ ቤቱ የመከራ ፅዋቸውን እየተጋቱ ነው። ይሄ የውርደት ታሪክ መቀየር ይኖርበታል።

የሠማያዊ ፓርቲ ፅ/ቤት ጥበቃ ሠራተኛ የ72 ዓመቱ አቶ ቀኖ አባጆቢርን ለእስር የዳረገ አገዛዝ ነው ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው።የ72 ዓመት ኢትዮጵያዊ ሽማግሌን አንኳ የሚፈራ ቡድን ነው አገሪቷን የተቆጣጠራት። አቶ ቀኖ የእለት ጉርሳቸውን ለመሸፈን ደመወዝ ተቆርጦላቸው የጥበቃ ሥራ የሚሰሩ እንጂ የፓሪት አባል አልነበሩም ሆኖም ግን ታፍነው ለእስር ተዳርገዋል። የህወሃቶች ግፍ ማብቂያ እና ወሰን አጥቷል።እነዚህ ቡድኖች እየፈፀሙ ያሉት ግፍ ጥላቻን እየወለደ፤ ቂምን እየተከለ ቀጥሏል። የህዝቡ ቂም እንደ ተዳፈነ እሳት የሚቀጣጠልበትን ግዜ እየጠበቀ ነው።ይህ ግዜ የመጣ ቀን ህወሃቶች እና አሽከሮቻቸው ወየውላቸው።ያ ግዜ ደግሞ ያለ ጥርጥር በእርግጠኝነት ይመጣል።ፈጥኖ እንዲመጣ በእኛ በኩል የሚቻለንን ሁሉ እያደረግን ነው።

ከህወቶች በተጨማሪ በዚያች አገር ታሪክ ውስጥ ፌዴራል ፖሊስ ተብለው የተደራጁት እና ከሰው መፈጠራቸውን የረሱ ቡድኖች መኖር በብርቱ ያሳስበናል። የፌዴራል ፖሊስ አባላት እየፈፀሙ ያሉት ጭካኔ አስገራሚ ነው። የዝህ ጦር አባላት ሰው ሁነው መፈጠራቸውን እስከንጠራጠር ድረስ አስገርመውናል። እንግዲህ የፌዴራል ፖሊስ አባላት ብዙ ግዜ ማሳሰቢያ ልከንላችኋል። አሁንም በተጨማሪ እንነግራችኋለን። ነገራችንንም ለታሪክ ይቆይ ዘንድ በመዝገብ እናኖረዋለን። አሁን የጭካኔ ሰይፋቸሁን መዛችሁ እንደ ፈለጋችሁ የምትገሏቸው ዜጎች ወገኖቻችሁ መሆናችሁን አትርሱ። ነገ ቢርባችሁ የሚያበሏችሁ፤ ብትወድቁ የሚያንሷችሁ፤ ብትጠሙ የሚያጠጧችሁ ዛሬ በያዛችሁት ጠመንጃ የምትገድሏችው ወገኖች ናቸው። እናንተ ግን ይሄን እውነት ለማየት አዚም የተደረገባችሁ ይመስላል።

ፌዴራል ፖሊሶች ታዝዤ ገደልኩ በማለት የምታመልጡ እንዳይመስላችሁ። ታዝዤ ገደልኩ ማለት ሥራየ መግደል ነው ማለት ነው። ሥራው መግደል የሆነ ማንም ይሁን ማን ወንጀለኛ ነው። ወንጀለኛ ደግሞ ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት መቀጣቱ አይቀርም። ስለሆነም የፌዴራል ፖሊስ አባላት በሰላማዊ መንገድ ኑሮ ተወወደብኝ የሚለውን ወንድማችሁን በቆመጥ ደብድቡ ስትባሉ አይ ሠላማዊ ሰውን እጠበቅ ዘንድ እንጂ እደበድብ ዘንድ ህግ አይፈቅድልኝም ማለት ስትችሉ ያገኛችሁትን ሁሉ እየሰበራችሁ መኖራችሁን እያየነው ነው። ይሄ በምንም መሥፈርት ትክክል አይደለም። አንዱ ታዝዤ ወንድምህን ወይም ልጅህን ወይም ደግሞ አባትህን ገደልኩ ቢልህ ምንድ ነው የሚሰማህ? መቸስ ታዘህ ነው እንግዲህ ምን ይደረጋል እንደማትል እርግጠኞች ነን። እኛ ሁላችን አንተ የፌዴራል ፖሊስ አባል በምትፈፅመው ጭካኔ በእጅጉ ተጎድተናል። የያዘከው ጠመንጃ የሸንበቆ ምርኩዝ የሚሆንበት ግዜ ወደ አንተ ፈጥኖ እየመጣ ነው። አሁን የያዝከው ቆመጥ ተሰብሮ ይወጋሃል በተወጋህ ግዜ ግን ዞር መግቢያ እንዳታጣ ለራስህ ተጠንቀቅ። አዛዦችህ እንደሆነ የአገሪቷን ንብረት ዘርፈው ወደ ውጭ አገር አሸሽተዋል፤ የቀረውንም በዘመድ አዝማዶቻቸው ሥም ብዙ ህንፃዎችን አሰርተው እየተዘባነኑበት ነው። አንተ ግን ከቀሪው ወገንህ ጋር ደም ትቃባለህ። ነገ ሌላ የተለየ አዲስ ቀን ነው። አዲስ ቀን በሆነ ግዜ መግቢያ እንዳታጣ አሁኑኑ ራስህን ከዘረኞች፤ ከዘራፊዎችና ከግፈኞች ጎን አግልለህ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን እንድትሰለፍ ደግመን ደጋግመን እንመክርሃለን። ይሄን ምክር አልስማ ካልክ ግን የሚመክርህ መከራ በደጅህ ፈጥኖ ይመጣል።

በመጨረሻም ህወሃቶችን ለማስወገድ የሚደረገው ትግል ተፈፍሞ መቀጠል የኖርበታል። ሁሉም በሚችለውና በሚያምነበት መንገድ ሳያቅማማ ይታገል። በሁሉም መንገድ የሚደረገው ትግል ፍሬ አፍርቶ በነፃነት እንደሚቋጭ ባለ ሙሉ ተስፋ ነን። እኛ የጀመርነውን ሁለ-ገብ ትግል አጠናክረን ተያይዘነዋል። ዕለት ዕለት እየጎለበትን እየሄድን ነው። አደረጃጀታችንም መሠረት ይዟል። ካሁን ወዲያ ትግላችንን የሚያቆም ምድራዊ ኃይል የለም። ነፃነታችንን ሳንቀዳጅ የጀመርነውን ትግል አናቆምም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !**

## ኦሮሚያ ዉስጥ የቂም በቀል ተኩስ ልውጥጥ የሦስት ሰዎችን ህይወት አጠፋ

በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በደራ ወረዳ ጉንዶመስቀል ከተማ ኗሪ የሆነ ከተማ ውብቱ የተባለዉን የዚሁ ከተማ ኗሪ የሆነዉን ሃብታሙ ሺበሺ በመሳሪያ ተኩሶ ከገደለ በኋላ ገዳዩን ለመያዝ በተደረገ ጥረት በአካባቢው ከፍተኛ የተኩስ ልውውጥ ተደርጎ ሦስት ሰዎች መገደላቸዉን ሰሜን ሸዋ ዉስጥ የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። ከተማ ውብቱ የተባለው ሰው በ1999 ዓ.ም. የሰዎች ለሰዎች የተባለውን ድርጅት ገንዘብ ከዘረፈ በሁዋላ ሃይማኖት ሺበሺ በተባለው ግለሰብ ቤት በአደራ ማስቀመጡን ተከትሎ ሃይማኖት ሺበሺ ገንዘቡን መካዱን የሚናገሩት የአካባቢው ሰዎች፣ ከዚህም በላይ ሃይማኖት ገንዘቡን አካፍልሃለው ብሎ ከተማ ውብቱን ከቀጠረው በሁዋላ በጥይት አቁስሎታል። ከተማ ውብቱ በቁጥጥር ስር ከዋለ በሁዋላ በዝርፊያ ተከሶ እንደነበር የሚናገሩት ነዋሪዎች፣ በ2003 ዓም ሃይማኖት መኪና ላይ ሲሳፈር ሲል መግደሉንና በመኪናው ዙሪያ የነበሩ 2 መምህራንና አንድ ሌላ ተሳፋሪ መሞታቸውን አክለዋል።

የሃይማኖት ወንድም የሆነው ሃብታሙ ሺበሺ እንዲሁም የሟቹ የቅርብ ዘመድ የሆኑት የፓርላማ አባሉ አቶ ለማ ተሰማ፣ አቶ ከተማ ውብቱን ለማስያዝ ላለፉት 4 ዓመታት ሲከታተሉት ቢቆዩም፣ ከተማ ውብቱና ደጉ አቢ የተባለ ግብረአበሩ፣ ሃብታሙ ሺበሺን ጉንዶ መስቀል ላይ ትናንት በጥይት ገድለውት አምልጠዋል።

ገዳዮችን አድነው ለመያዝ የወረዳው ፖሊስ አባላት፣ የወረዳው የሚሊሺያ አባላትና የዞን አድማ በታኞች አሰሳ ያደረጉ ሲሆን፣ ካቢ ቀበሌ ውስጥ መሸጎ የነበረውን ደጉ አቢን አራት የእጅ ቦንቦች በመወርወር ሲገድሉት፣ ከከተማ ውብቱ ጋር ደግሞ ለረጅም ሰአታት የቆየ የተኩስ ለውውጥ ተካሂዷል። በተኩስ ልውውጡ መሃል የአድማ ብተና ሃላፊው ሲገደል አንድ ሌላ ፖሊስ ደግሞ በጽኑ ቆስሎ ሆስፒታል ተኝቷል። ገዳዩ ከተማ ውብቱም ከሌሊቱ 11 ሰዓት መገደሉን የአካባቢው ምንጮች ገልጸዋል።

## መሪዎቻቸዉ ቢታሰሩም ትግሉ እንደማይቆም የ 9 ፓርቲዎች ትብብር አስታወቁ

የምርጫ ስርዓት ለውጥ እንዲደረግ ለመጠየቅ ህዳር 27 ቀን የአዳር ተቃውሞ ሰልፍ ለማድረግ ወደ አደባባይ በወጡት 9 የተቃዋሚ ድርጅት አመራሮች ላይ የፌደራል ፖሊስ አባላት ድብደባ በመፈጸም ወደ እስር ቤት ቢወስዱዋቸውም፣ የትብብሩ አመራሮች ግን ትግሉ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልና ኢትዮጵያውያን ለትግሉ የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጠይቀዋል።

ሶስተኛ እየተባለ በሚጠራው እስር ቤት ውስጥ ታስረው የሚገኙት የትብብሩ ሊቀመንበር ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት፣ አቶ ኤርሚፎ ኤርዳሎ፣ አለሳ መንገሻና ሌሎችም አመራሮች አራዳ ምድብ ችሎት ቀርበው የ14 ቀን የጊዜ ቀጠሮ ፣ በጨርቆስ ታስረው የሚገኙት እነ አቶ ግርማ በቀለ ደግሞ የ7 ቀን የጊዜ ቀጠሮ ተጠይቆባቸዋል። አመራሮቹ ህግመንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድና የተከለከለ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ወንጀል መከሰሳቸውን ታውቋል።

በፍርድ ቤት አካባቢ ሆነው ጉዳዩን ከተከታተሉት መካከል ናትናኤል ያለምዘውድ ለኢሳት ሲናገር፣ አብዛኞቹ አመራሮች ሲሄዱ ያነክሱ እንደነበር ገልጾ፣ ኢ/ር ይልቃል እጁ አካባቢ መመታቱን፣ ብርሃኑ ተክለያሬድ ደግሞ እጅና እግሩ አካባቢ በጨርቅ ተጠቅሎ ማየቱን ገልጿል። ሴት እስረኞችም ሲጓዙ ያነክሱ እንደነበር በተለይ አንደኛዋ ኩላሊቷ አካባቢ መመታቱዋን እንደገለጸችለት ተናግሯል ሴት እስረኞችን ለመጠየቅ በሄደበት ወቅት ለአጭር ደቂቃዎች ራቅ ብሎ ለማናገር መቻሉን የገለጸው ዮሴፍ ተሻገር በበኩሉ፣ ሴቶቹ በጠንካራ መንፈስ ላይ እንደሚገኙ ገልጿል።

ኮተቤ አካባቢ ታስረው ስለሚገኙት የድርጅት መሪዎችና አባላት ጉዳይ በስፍራው በመገኘት ለመታዘብ የቻለው አቶ አምላኩ ፍሰሃ እንደገለጸው ደግሞ ምንም እንኳ እስረኞቹ መጸዳጃ ቤት አካባቢ በመታሰራቸው እንዲሰቃዩ ቢደረግም አሁንም በጠንካራ መንፈስ ላይ መሆናቸውን ገልጿል። መንግስት የወሰደው እርምጃ በትብብሩ የወደፊት የትግል አካሄድ ላይ ተጽእኖ ይኖረው እንደሆን የተጠየቁት የመኢዴፓ ሊቀመንበርና የትብብሩ ገንዘብ ያዥ አቶ ኑሪ ሙዲሰር ሲመልሱ “ መንግስት እስረኞች ይፈቱ አይፈቱ ወደ ሚል አታካራ እንድንገባ ቢፈልግም፣ እኛ ግን ትግሉን ወደ ፊት ከመግፋት ውጭ ሌላ አማራጭ የለንም” ብለዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የዘጠኙ ፓርቲዎች ትብብር የኢትዮጵያ ህዝብ ከወያኔ ጋር ለሚደረገዉ ትግል አስፈላጊውን አስተዋጽኦ እንዲያደርግና ትግሉን ሙሉ በሙሉ እንዲቀላቀል ጥሪ አድርጓል። በሌላ በኩል ደግሞ አንድነት ፓርቲ በ9 ፓርቲዎች ላይ የተወሰደውን እርምጃ አውግዟል። ፓርቲው ባወጣው መግለጫ “የዘጠኙ ፓርቲዎች አመራሮችና አባላት በህገ መንግስቱ ላይ የተቀመጠውን ሰላማዊ ሰልፍ የማድርግ መብት ከመጠቀም ውጪ ያጠፉት ምንም ዓይነት ነገር ስለሌለ በአስቸኳይ ሊፈቱ ይገባል።” ብሎአል። ፓርቲው “የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ይህ ህገወጥና አረመኔያዊ ድርጊት በዝምታ ሊያልፈው አይገባም፤ ኢህአዴግን በቃህ ሊለው ይገባል።” በማለት በመግለጫው አስታውሷል።

## የወያኔ ዘረኛነት ያንገፈገፋቸዉ ሰባ ኢትዮጵያዉያን ቀይ ባህር ዉስጥ ሰጥመዉ ህይወታቸዉ ማለፉ ተሰማ

ዘረኛዉ የወያኔ ስርዐት ስልጣን ከያዘበት ግዜ ጀምሮ የወያኔን እስርና ግድያ እየሸሹ አገራቸዉን ለቅቀዉ የሚሰደዱ ሰዎች ቁጥር በየቀኑ እየጨመረ ሲሆን በተለይ በየበረሀዉ፤ በየወንዙና በቀይ ባህር ላይ በሚደረገዉ የስደት ጉዞ ህይወታቸዉ የሚያልፍዉ ወገኖቻችን ቁጥርም የዚያኑ ያክል እየጨመረ መሆኑን ብዙ አለም አቀፍ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ። የስደት ጉዞ ይዞት የሚመጣዉን ከፍተኛ መከራና የሚያስከፍለዉን የህይወት መስዋዕትነት ስደትን የሚያስብ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚረዳዉ ቢሆንም ከወያኔና ከዘረኛ ስርዐቱ የማይሻል ነገር የለም እያሉ ብዙ ኢትዮጵያዉያን የቀይ ባህርና የሰሃራ በረሃ ዉስጥ እንደወጡ ቀርተዋል። ሰሞኑን ወደ የመን ሲጓዝ የነበረ ጀልባ ሰጥሞ ከ79 ያላነሱ ኢትዮጵያዊያን ያለቁ ሲሆን እስካሁን የ14 ያልበለጡ ሰዎች አስከሬን ብቻ መገኘቱን ጋዜጠኛ ግሩም ተክለሃይማኖት ገለጸ። እንደ ጋዜጠኛ ግሩም አገላለጽ የሟቾቹ ቁጥር በተለያዩ የዜና ማሰራጫ ተቋሞች እንደተገለጸዉ ሳይሆን ቀይ ባህር ዉጦ ያስቀራቸዉ ኢትዮጵያዉያን ቁጥር 79 መሆኑን አክሎ ተናግሯል።

በሌላ በኩል ደግሞ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሕጋዊ ጉዞን ከአንድ ዓመት በላይ አግዶ በመቆየቱ በየጊዜው ለሚሞቱ ሰዎች ምክንያት መሆኑን ምንጮች ገልጸዋል። በመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት በሚሄዱ ኢትዮጵያዊያን ላይ የሚደርሰው የሰብዓዊ መብት ጥሰት መባባስ አሳስቦኛል በሚል በጥቅምት ወር 2006 ዓ.ም ላልተወሰነ ጊዜ እንዲቆም የተደረገው የውጭ ሀገር ስራ ስምሪት፣ ሕገወጥ ሥራው ይበልጥ እንዲጠናከር መንገድ መክፈቱን ያስታወሱት ምንጮቹ በዚህ ምክንያት በዜጎች ላይ የሚደርሰው እንግልትና መከራ በአሳዛኝ መልኩ ተጠናክሮ መቀጠሉን ይናገራሉ።

ሰሞኑን ወደየመን ሲጓዙ ያለቁት ወገኖችም ለዚህ ችግር የተዳረጉት ሕጋዊ መንገዱ ስለተዘጋባቸው መሆኑን አስታውሰው ለዚህ ክስተት ደግሞ የኢህአዴግ መንግስት ሃላፊነቱን ሊወስድ እንደሚገባ ተናግረዋል። በተያዘዘ ዜና ወደ አረብ ሀገራት ለስራ በሚሄዱ ዜጎችን ላይ እየደረሰ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት ለመቀነስ አስተዋጽኦ ይኖረዋል በሚል የተረቀቀውና በዚህ ዓመት በፓርላማ ጸድቆ ወደስራ ይገባበታል የተባለው፣ አሁን በስራ ላይ ያለውን የግል ሥራና ሠራተኛን የማገናኘት አዋጅ ቁጥር 632/2001 የሚያሻሽለው ረቂቅ አዋጅ ገና በረቂቅነቱ ውዝግብ ገጥሞታል። ረቂቅ አዋጁ ከስምንተኛ ክፍል በታች ያሉ ዜጎች ወደአረብ ሀገራት መሄድ እንደማይችሉ መደንገጉ ሕገወጥ መንገዱን ለማጠናከር የሚረዳ ነው በሚል ተቃውሞ ገጥሞታል።

አሁን በሥራ ላይ ባለው አዋጅ ቁጥር 632/2001 መሰረት ከ 400 በላይ ሥራና ሠራተኛን አገናኝ ኤጀንሲዎች ተቋቁመው ባለፉት ዓመታት ኢትዮጵያዊያን የቤት ሠራተኞችን ወደተለያዩ የአረብ ሀገራት ሲያስቀጥሩ የቆዩ ቢሆንም በአለማቀፍ ጫና ምክንያት መንግስት ጉዞውን በማገድ ሕጉን ለማሻሻል እየሰራሁ ነው በማለት መግለጹ ይታወሳል። የጉዞ እገዳው ከተጣለ ከአንድ ዓመት በላይ ያስቆጠረ ሲሆን አብዛኛዎቹ ኤጀንሲዎች ሥራው ከመቋረጡ ጋር ተያይዞ ለቤት ኪራይና ለሠራተኞች ደመወዝና ለሌሎች አላስፈላጊ ወጪዎች በመዳረጋቸው ሥራውን ለመተው፣ አንዳንዶቹም ለመቀየር መገደዳቸው ታውቋል። በዚሁ የአዋጅ ማሻሻያ መሰረት በመንግስት ደረጃ ስምምነት ወደሌለባቸው ሀገራት ሠራተኞችን መላክ የሚከለከል ሲሆን የሚላኩ ሠራተኞችም ቢያንስ የስምንተኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ ሊሆኑ እንደሚገባ ደንግጓል። አንዳንድ ሠራተኞችን የሚልኩ ኤጀንሲዎች ይህ ረቂቅ አዋጅ በተለይ በትምህርት ላይ ገደብ ማበጀቱ ሕገወጥነት ... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፤ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የአለም ህዝብ በነዳጅ ዋጋ ማነስ ሲንበሸበሽ አዲስ አበባ የነዳጅ ያለህ እያለች ነዉ

የአለም ህዝብ በከፍተኛ ፍጥነት እየቀነሰ በመጣዉ የነዳጅ ዋጋ ተጠቃሚ በሆነበት በአሁኑ ወቅት የፈረደበት የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ነዳጅ ብርቅ እንደሆነበት አዲስ አበባና በየክልሉ የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን የላኩልን ዜና ያስረዳል። አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን በአራት ኪሎ፣ በቦሌ፣ በካዛንቺስ፣ በልደታ አካባቢዎች የሚገኙ ነዳጅ ማደያዎችን ተዘዋውረዉ እንደተመለከቱት በየነዳጅ ማደያዉ ከፍተኛ የተሽከርካሪዎች ብዛት መታየቱንና የትራፊክ መጨናነቅ መኖሩን ለማየት ችለዋል። በዓለም ገበያ ላይ የነዳጅ ዋጋ መቀነስን ተከትሎ የአገዛዙ ንግድ ሚኒስቴር መጠነኛ የነዳጅ ዋጋ ቅናሽ ቢያደርግም ይህ ችግሩን እንዳልቀረፈዉ ለማወቅ ተችሏል።

ሚኒስቴሩ በነዳጅ ምርቶች ላይ በየወሩ መጨረሻ ክለሳ የሚያደርግ ሲሆን እስከዛሬ በነበረው የተለመደ አሰራር ወይ ይጨምራል፤ ወይንም ባለበት እንዲቀጥል ሲያደርግ ቆይቷል። በአለም ገበያ ላይ በከፍተኛ መጠን ያለውን ቅናሽ መሰረት በማድረግ ባለፉት 15 ቀናት ጊዜ ውስጥ የነዳጅ የችርቻሮ ዋጋ ሲቀንስ ይህ ለሁለተኛ ጊዜ ነው።ሆኖም ማደያዎቹ የዋጋ ቅናሽ ሲደረግ በስቶክ ውስጥ ያለ ምርታቸው ቀደም ባለ ዋጋ የገዙት በመሆኑ እንደማያዋጣቸው በመግለጽ ላለመሸጥ አንገራግረው የነበረ ቢሆንም ንግድ ሚኒስቴር ባደረገው ጫና በሙሉ ወደስራ ሊመለሱ ችለዋል። ካለፉት ስድስት ወራት በፊት የነዳጅ ዋጋ በበርሜል 115 የአሜሪካ ዶላር የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ወደ 67 የአሜሪካ ዶላር ያሽቆለቆለ መሆኑ ይታወቃል። በአዲስአበባ ባለፉት ሶስት ቀናት የተፈጠረውን የነዳጅ እጥረት በዛሬው ዕለት ተባብሶ በአብዛኛዎቹ ማደያዎች በተሽከርካሪዎች ወረፋ ተጨናንቀው ዋሉ።

## የወያኔ ዘረኛነት ያንገፈገፋቸዉ ሰባ ኢትዮጵያዉያን ቀይ ባህር

. . . ( ከገጽ 4 የዞረ )

እንዲስፋፋ ያደርጋል በማለት አንቀጹ እንዲነሳ ከወዲሁ እያሳሰቡ ነው። ከአንድ ዓመት በላይ በእገዳ ላይ የቆየው የውጭ ሀገር የስራ ስምሪት መቼ ተነስቶ ሥራው እንደሚጀመር አሁንም የታወቀ ነገር እንደሌለ የጠቆሙት ምንጮቻችን በዚህ ምክንያት ሕገወጥ ጉዞው ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ተጠናክሮ መቀጠሉ በከፍተኛ ደረጃ አሳሳቢ መሆኑን አመልክተዋል።

## ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ይህ በእንዲህ እንዳለ በውጭ አገራት በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በዜጎች፣ በፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና አባላት ላይ የወሰደውን አረመኔያዊ እርምጃ ማለትም አፈና፣ ድብደባና የጅምላ እስር ለማውገዝና ለትብብሩ ያላቸውን ድጋፍ ለማድረግ የተቃውሞ ሰልፎችን ለማድረግ እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን ምንጮቻችን አመልክተዋል። ከነዚህም የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች አንዱ የሆነው ትላንት november 8 ቀን 2014 በአሜሪካ ዋሽንግተን መካሄዱን ያደረሱን ምንጮቻችን በዕለቱ የተቆጡት ኢትዮጵያውያኑ በዋሽንግተን ዲሲ የነበረው ቀዝቃዛ አየርና በረዶ ሳይብግራቸው ፋሺስታዊው አገዛዝ በ9ኙ ፓርቲዎች ትብብር አመራሮችና አባላት እንዲሁም በተቃውሞው ለመሳተፍ በወጡ ኢትዮጵያውያን ላይ የወሰደውን እጅግ አረመኔያዊ ድብደባና የጅምላ እስር ማውገዛቸው ታውቋል። አድማጮቻችን በዚህ አጋጣሚ በሌሎችም የአለም ዳርቻዎች የሚደረጉ ተመሳሳይ የተቃውሞ ሰልፎችን እየተከታተልን እንደምንዘግብ ከወዲሁ ለማሳሰብ እንወዳለን።

## ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች እርስ በርስ ተፋጥጠዋል

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በተያያዘ ዜና ከመቼውም ጊዜ በላይ የሕወሐት ሕልውና አጣብቂኝ ውስጥ በገባበት በአሁኑ ወቅት በሌላ ጐራ የተነሱ ወጣት የፓርቲው ካድሬዎች፤ ሁሉም አንጋፋ አመራሮች ከድርጅቱ እንዲለቁ ጥያቄ ማቅረብ መቀጠላቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ቡድኑ ለዚህ ጥያቄ አፋጣኝ ምላሽ ሊሰጥ ካልቻለ ወይንም ይህን ለማድረግ ፈቃደኛ ካልሆኑ ግን ሕወሐት ሊፈርስ እንደሚችል ማስጠንቀቂያ አዘል ዛቻ መስጠታቸውን ምንጮቻችን አያይዘው ገልፀዋል። በድርጅቱ ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየነገሰ ያለውን ሽኩቻና መፈረካከስ ተከትሎ በርካታ ሹማምንቶች አገዛዙን በመክዳት በተለያዩ የአውሮፓና አገራት እንዲሁም በአሜሪካ የጥገኝነት ጥያቄ እየጠየቁ እንደሚገኙ የሚታወቅ ሲሆን ከሰሞኑ ተቀማጭነታቸውን በደ. ኮሪያ ያደረጉ ሁለት ዲፕሎማቶች አገዛዙን በመክዳት በአሜሪካ የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቃቸው ታውቋል። በአገር ቤት የሚኖሩ ቁጥራቸው ቀላል የሚሉ ሹማምንትም በዘረፋ ያከማቹትን የአገር ሃብት እያሸሹ እንደሚገኙና ስርአቱን ለመክዳት ለማምለጥ ሁኔታዎችን በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኙም ለማወቅ ተችሏል።